የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

ቁጥር አ1162/11/812

ቀን ታኅሣሥ 14 ቀን 2015 ዓ.ም.

**ለአማራ ብሔራዊንቅናቄ (አብን)**

**<u>አዲስ አበባ</u>፣**

**ጉዳዩ፡- <u>የፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤን ይመለከታል</u>፤**

ፓርቲው ታኅሣሥ 3 ቀን ዓ.ም. በቁጥር አብን 436//15 እና ታኅሣሥ 10 ቀን ዓ.ም. በቁጥር አብን 437/02/15 በተፃፉ ደብዳቤዎች 3ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤውን ለማድረግ ቅድመ ጉባኤ ሥራዎችን ማጠናቀቁን ገልፆ ጉባኤው ታኅሣሥ 22 እና 23 ቀን 2015 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ ለማድረግ መወሰኑን ለቦርዱ አሳውቋል።

ቦርዱ የቀረበውን ጥያቄ ሰኔ 3 ቀን 2010 ዓ.ም. ከፀደቀው የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ አንፃር መርምሯል። በዚህ ደንብ አንቀፅ 12(15) የፓርቲው ብሔራዊ ምክር ቤት መደበኛ፣ ልዩ እና አስቸኳይ ስብሰባዎችን የመጥራት እንዲሁም የጉባኤ አዘጋጅ ኮሚቴም የማቋቋም ሥልጣን ያለው መሆኑ ተደንግጓል።

የብሔራዊ ምክር ቤቱ አባላት በዚሁ የፓርቲው ደንብ አንቀፅ 12 (1) መሠረት 45 መደበኛ እና 13 ተለዋጭ መሆናቸው፤ አባላቱ ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ እንደሚሟላ፤ ስብሰባዎችም የሚያልፉት ከግማሽ በላይ የሆኑት የምክር ቤቱ አባላት ሲገኙ መሆኑን በአንቀፅ 27 (1-2) ደንግጓል። ይሁንና የፓርቲው ብሔራዊ ምክር ቤት ነሐሴ 7 ቀን 2014 ዓ.ም. በአደረገው ስብሰባ ላይ ከተገኙት 22 ተሰብሳቢዎች መኃል 8 ብቻ የብሔራዊ ምክር ቤት አባላት መሆናቸውን ቦርዱ ተረድቷል።

በመሆኑም ታኅሣሥ 22 እና 23 ቀን 2015 ዓ.ም. ይደረጋል የሚባለውን የጉባኤ ስብሰባ እንዲካሄድ የፓርቲው ብሔራዊ ምክር ቤት ውሣኔ የሰጠው የምክር ቤቱ ምልአተ ጉባኤ ሳይሟላ መሆኑን ከፓርቲው ከቀረቡለት ሰነዶች ቦርዱ ተረድቷል።

ስለዚህ ከላይ በዝርዝር በተገለፁት የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ ድንጋጌዎች መሠረት ብሔራዊ ምክር ቤቱ ነሐሴ 7 ቀን 2014 ዓ.ም. በወሰነው ውሣኔ መሠረት ይህን ጠቅላላ ጉባኤ መጥራትና ማካሄድ የሚችልበት የሕግ አግባብ የሌለ መሆኑን በአክብሮት ልንገልፅ እንወዳለን።

ከአክብሮት ሠላምታ ጋር

ውብሸት አየለ ጌጤ
Woubshet Ayele Gete
ኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ምክትል ሰብሳቢ
Deputy Chairperson National Electoral Board

ለድምጽዎ የሚያምኑን

ፌስቡክ
/national-electoal-board-of-ethiopia-nebe

ትዊተር
@NEBEthiopia

ኢሜይል
contact@nebe.org.et

ድረ-ገጽ
www.nebe.org.et

አድራሻ - ቦሌ ክፍለሚገንን
ሬስቶራንት ገባ ብሎ በስተቀኝ
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

ስልክ
+251 115 153468

ፋክስ
+251 115 510025